# ብርትኳን የምትፈታበት ቀን ተተነበየ

ከጥቂት አመታት በፊት እንዲህ አይነት ቀልድ ነበር ….. የአንድ መንደር ሰዎች ዝሆን እርሻቸውን እያበላሸ ቢያስቸግራቸው አቤት ለማለት ወደ በላይ መሄድ እንዳለባቸው ስምምነት ላይ ይደርሳሉ። በስብሰባ ወቅት ጥቃት በቃን እስከመቼ ዝም እንላለን እያሉ የሚያቅራሩ በረከቱ። እንፋለማለን! አደን እንወጣለን! የሚሉ እለቱኑ ዝሆኑን ለመግደል ዝግጁ መሆናቸውን እየገለጹ ቁጣቸውን ለማሰማት ሽለሉ ፎከሩ። በመጨረሻም የሚሻለው አገረገዢው ዘንድ ድረስ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣትና አስቸኳይ መፍትሄ መጠየቅ ነው ተባባሉና  ወደ ሀገረ ገዢው ቢሮ አቀኑ።  ወደ ቢሮው አካባቢ ሲደርሱ ድምጻቸው እየሰለለ መዝሙሩም ፉከራውም ቀረርቶውም ሁሉ ወደ ማጉረምረም ተለወጡ። የቢሮው ቅጥር ጊቢ ሲደርሱ ወደ ቀብር የሚሄዱ ይመስል አንገት ደፍተው ጸጥ ብለው ነበር። በመጨረሻም አገረ ገዢው እየተንጎማለሉ ቆጣ ብለው… "ምን ችግር ተፈጠረ? ምን ሆናችሁ ነው የተሰበሰባችሁት?" ብለው በቁጣ ሲናገሩ ማን መልስ ይስጥ ማንስ ይናገር። "…. አንተ ተናገር አንቺ ተናገሪ" እየተባባሉ መጎሻሸምና መጠቋቆም ቀጠሉ። በመጨረሻም አንዱ ተነስቶ "… ጌታዬ በአገር ሰላም… ባልጠፋ መሬት አንድ ዝሆን ብቻውን እንዴት ይኖራል? ዝሆን ብቸኝነት ጎድቶታል። ገራም እንሥሳ ነው ብሎ ሲጮህ። ሌሎቹም ተቀብለው "… አዎን ዝሆን ገራም ነው" ማለት ጀመሩ። "ዝሆን ጥሩ!" ሲል ሌሎችም  "ዝሆን ጥሩ!" ዝሆን በጣም! ዝሆን በጣም እያሉ መፈክር ያሰሙ ጀመር። የፈሪ ነገር አንድ ዝሆን ለማሳገድ ሄደው ዝሆን ይጨመርልን ብለው ተመለሱ። የኛም ነገር እንዲህ ነው። መከራ ጨምሩልን! ሀዘን አብዙልን የምንል ይመስላል።

በሻማ የማብራት ከፍተኛ ትንቅንቅ ከአንድነት ወደ መድረክ ያሻቀበው ድርጅት ወያኔን በምርጫ ሲያሸንፍ ወይዘሪት ብርትኳን ከእስር እንደምትፈታ ተነበየልን። ሰላማዊ ትግል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር ዘገምተኛ መሆኑን አበክረው አስገንዝበውን በአንድና ሁለት አመት ውስጥ ውጤት መጠበቁን ትተን ትዕግስት እንድንሰንቅ መከሩን።  ብርትኳን መራሹ የተቃዋሚ ድርጅት ይህን ካለን መለስም ከስልጣን የመውረድ ሀሳብ ስለሌለው ብርትኳን  ቃሊቲ ውስጥ ልታረጅ ነው ማለት ነው። ይህን ስንመለከት የብርትኳን ጉዳይ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነና ከነማን ጋር ለትግል እንደተሰለፈች ልብ እንድንል ያስገነዝበናል። አቶ አስራት ጣሴ ወያኔዎች 'immotional, irrational and most illogical' መሆናቸውን ጠቅሰዋል። በምርጫ እንደሚያሸንፉ ደግሞ ሲያስረዱ በዋሻው መጨረሻ ብርሀን መኖሩንና የተስፋ ሰው መሆናቸውን አክለው ማብራርያ ሰጥተዋል። እንግዲህ ይህን ግንፍል ወይም ስሜታዊ አመክንዮ የማይገባውና ሚዛናዊነት የጎደለውን የወያኔ ቡድን በነጻነት መሰብሰብ እንኳ ሳይችሉ በምርጫ አሸንፈን ብርትኳንን እናስፈታለን ሲሉ የእርሳቸውና የአጋሮቻቸው 'ሎጂክ' ግራ የገባው መሆኑ ግልጽ ነው።

ብርትኳን እውነትን ላለማዋረድ፣ ቃልዋን ላለማጠፍና ለጉልበተኞች ላለማጎብደድ ስትል እንጂ ዝናና ክብር ፍለጋ ወደ እስርቤት አልገባችም። እስርቤት ሳትገባም ዝናና ስም የነበራት ናት። አንድ ፓርቲ በግፍ የታሰረች መሪውን ማስፈታትን የመጀመርያ ግዴታው ካላደረገ እንዴት ነው ለሕዝብ ነጻነት የሚታገል? ለድርጅቱ ሲሉ የታሰሩና የተደበደቡ ገበሬዎች ምን ይበሉ? ዛሬስ አንድነትን ወግነው ያሉ ወጣቶችስ ምን ይሰማቸው? ለብርትኳን እንኳ ደንታ ባይኖራችሁ እንደፖለቲካ ታክቲክ መሪ የማስፈታትን ጉዳይ ግንባር ቀደም መደራደርያ ማድረግ የግድ አስፈላጊ መሆን የነበረበት ይመስለኛል። ይህ በከፊል እርዳታ ለጋሽ አገሮች በሚያደርጉት ተጽእኖ ተቀባይነት ያገኘ የሚመስለው 'መሪያችንን ማስፈታት 'ከድል በሁዋላ' አይነት አባባል በእጅጉ የተሳሳተ መንገድ ነው። ዛሬ በብርትኳን ላይ የዚህን አይነት አመለካከት ይዘው የሚሄዱ ሰዎች ነገ እብሪተኛው ወያኔ አንቆ ከእስር ቢጨምራቸው የዘሩትን ማጨድ ይሆን ዘንድ እውነት ነው።

ምንም እንኳ በርካታዎቻችን መተቸት እንጂ ገብቶ መስራት የማንችል የአገርን መፍረስ ዳር ቆመን የምንመለከት ብንሆንም መሪ ነን የሚሉን ደግሞ እንዲህ አይነት መንገድ ሲመርጡ ማየት እጅግ አሳሳቢ ነው። አቶ አስራት እንዳሉት ከወዲህኛው የዋሻ ጫፍ ሆነን በወዲያ የምናየው ብርሀን በዚሁ ከቀጠልን የወዲያኛው መውጫ ኢትዮጵያ መሆኑ ቀርቶ ሱዳንም ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳ ጥያቄውን እንዳልሰሙ ቢያልፉትም አገሪቱን እያዳረስን ነው የሚሉን ከሆነ ተገምሶ ወደሱዳን የሚገባው የአገሪቱ ክልል ያሳሰባቸው አይመስልም ወይም የሚያውቁት ጉዳይ የለም። አገር እየተሸጠ ባለበት ጊዜ እንዴት ነው አንድ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ያገባኛል የሚል የፖለቲካ ድርጅት ይህን በዝምታ የሚመለከት? ከዚህ መንግስት ጋርስ እንደምን ተደራድሮ ነው ወደ ምርጫ የሚገባው? ምን ይዞስ ነው የሚደራደረው? ካልፈለጋችሁ ገደል ግቡ ብሎ በግልብ ምላስ ቢሰድባቸው እንኳ እንግዲያውስ እንዲህ እናደርጋለን የሚሉት ነገር የለም። ወያኔ መድረክን ምኑን ፈርቶ ነው

ለድርድር የሚቀርበው። እንደቀድሞው መልኩን ሊያሳምርበት እንጂ። ምናልባትም ለዲፕሎማቲኮቹ የቃለጉባዔ ሽፋን መስጫ ካልሆነ በቀር አሁን ባለው ሁኔታ የትኛውም ድርጅት ለድርድር አቅሙን አላጎለበትም።

የብርትኳን ጉዳይ ለመደራደርያ ትልቅ ኃይል ይሆን ነበር በዚህ ዙርያ ብዙ ስራ ተሰርቶ ቢሆን ኖሮ። አቶ አስራት "ያለንበትን ሁኔታ አታውቁትም መከራ ነው ስቃይ ነው" ብለውናል። እንግዲያው የሰላማዊ ትግል ለማድረግ ሁሉም ሁኔታ ተዳፍኗል ብለው መደምደም ይችሉ እንደሆን እንጂ በወር አንዴ ሻማ እያበሩ ለብርትኳንና ለኢትዮጵያ ፍትህ እናመጣለን ማለት ከንቱ ህልም ነው።

አንድነት በመድረክ ይጠነክራል፣ አንድነት በመድረክ ይጎለብታል እንጂ አይኮስስም ብለውናል። ሀቁ ግን አንድነት ወደ መድረክ በመምጣቱ የጎለበተበትን ሳይሆን መሪውን አስበልቶ የኮሰሰበትን ነው የተመለከትነው። በማነሱም ነው የታላቅ መሪውን በግፍ መታሰርዋ ያብቃ ማለቱ ከብዶት ወደ ምርጫ ለመግባት መንደርደሩን የተያያዘው።

ስለዚህ ይህ በከፍተኛ ደረጃ አነጋጋሪና አሳሳቢ የሆነን ጉዳይ በሚገባ ትኩረት ተሰጥቶበት አባላቱን የማያስቆጣ ደጋፊዎቹን የማያርቅ እንዲያም ብሎ የድሉን ቀን የማያርቅብን ተግባር ይከናወን ዘንድ ለማሳሰብ እወዳለሁ። ከጀርመን፣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ከተውጣጡ ዲፕሎማቶች ይልቅ ጉዳዩ የሚያገባቸው ኢትዮጵያውያን የሚሉት ይበልጣል። የሰላማዊው መንገድ ሙሉ በሙሉ ከተዘጋበት፣ አንዳችም ስንዝር እልፍ ለማለት ካልተቻለ የትግሉ ስልት መልኩን ቢቀይር ስህተት የለውም። ሚዛን የሚደፋ ቀልብ የሚስብ ከሰላማዊ ትግል አንጻር አንድ ሁለት ሊባል የሚችል ሥራ ለመስራት ካልተቻለ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ ትግሉን መልክ ማስያዝ ቀዳሚ ተግባር ሲሆን መሪውን ማስፈታት ደግሞ ለድርጅቱ ሕልውናም ወሳኝ ነው። ስለዚህ አንድነት እንደ ድርጅት እያደረገ ያለውን ተጋድሎ እያደነቅሁ ቀናውን መንገድ ይመርጥ ዘንድ ደግሞ ምኞቴ ነው።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com